DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS




www.dcps.dc.gov

ጥያቄዎች አሉዎት? በቀጣዩ አድራሻ ያግኙን
(202) 719-6613 ወይም ofpe.info@dc.gov.
1200 First Street, NE, Washington, DC 20002

/dcpublicschools @dcpublicschools @dcpublicschools

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የወላጅ ስርዓተ ትምህርት መምሪያ



# የክፍል ደረጃ 3



# የወላጅ ስርዓተ ትምህርት መምሪያ የአጠቃቀም መንገድ፥

ይህ መምሪያ ልጅዎን በቤት ውስጥ ለማገዝ የሚያስፈልጉዎትን መሳሪያዎች ይሰጥዎታል። በዚህ የመረጃ ጥራዝ ውስጥ፣ ልጅዎ የትምህርት ግቦቹን እንዲያሳካ ለማገዝ እንዲችሉ በ DCPS ስርዓተ ትምህርት ላይ የተመሰረቱ ስትራቴጂዎችን ያገኛሉ። ልጅዎ በት/ቤት ውስጥ የሚማረውን ትምህርት እና በተጨማሪም በቤት ውስጥ እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ጥሩ ግንዛቤ ይጨብጣሉ/ያገኛሉ።

## እርስዎ ማድረግ የሚችሉት፥

በልጅዎ አካዳሚክ ብቃት ላይ እርስዎ ወሳኝ ሚና ይጫዎታሉ። በቤት ውስጥ ጥሩ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ እነዚህ የተወሰኑ አስፈላጊ ነጥቦች ናቸው፡

- ትምህርት የስኬት መሰረት መሆኑን ልጅዎ እንዲያውቅ ያድርጉ።
- ልጅዎ 3ኛ ክፍል ውስጥ ምን ይማራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ይወቁ።
- ልጅዎ ከፍተኛ የሆኑ የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ አካዳሚያዊ ግቦችን እንዲያሰቀምጭ ያግዙት።
- የቤት ስራ በተገቢው ሰአት እና በአግባቡ እንዲያጠናቅቅ በቂ ጊዜ ይስጡ።
- በት/ቤት ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ከልጅዎ ጋር በመነጋገር ሒደታዊ ለውጦችን ያለማቋረጥ ይከታተሉ።
- ለልጅዎ ይሟገቱ።
- የልጅዎን ጥንካሬ ከመምህሩ ጋር ይጋሩ።

## የልጅዎን መምህር መጠየቅ የሚያስፈልጉ ጥያቄዎች፥

ከልጅዎ መምህር ጋር በሚወያዩበት ጊዜ ስለ ልጅዎ የትምህርት አቀባል እና ሁኔታ ላይ ትኩረት እያደረጉ ቀጥሎ የተመለከቱትን ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡

- የመማር ግቦች ምንድን ናቸው? የመማር ግብ አስመልክቶ ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች እንደ ምሳሌ ሊነግሩኝ ይችላሉ?
- የልጄን ስራ እንደ ምሳሌ ማየት እችላለሁ? እነዚህን የመማር ግቦች የሚያሳካው ወይም የማያሳካው እንዴት ነው?
- ልጄ በትምህርቱ እያለ/ ከሆነ ደረጃ በላይ ሲዘልቅ ሌላ ተጨማሪ ድጋፍ ማድረግ የሚገባኝ ምንድናቸው? ቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላሁ?
- ቤት ውስጥም መተግበር ያለባቸው የመማሪያ ክፍል ውስጥ መደበኛ ተግባራት ምንድን ናቸው?
- የእርስዎን ክፍለ ጊዜ በተመለከተ ለልጄ በየቀኑ ማቅረብ ያለብኝ ጥያቄዎች ምን ዓይነት ናቸው?

## ከልጅዎ ጋር መነጋገር፥

ጥሩ ጭውውቶች ልጆቻችነ በሕይወታቸው ውስጥ እኛ እንደሚያገባን እንዲያዩ ያግዛሉ። እነዚህ ከልጆችዎ ጋር መልካም ውይይት በሚያደርጉበት ጊዜ በቅድሚያ መጠየቅ የሚያስፈልጉ ጥያቄዎች፡

- እስኪ በቀንህ ውስጥ ምርጥ ስለምትለው ጊዜ አውራኝ።
- በውሎህ ውስጥ ያጋጠመህ እጅግ በጣም ፈታኝ ነገር ምንድነው?
- ዛሬ ከተማራችሁት ውስጥ አንድ ነገር ልታሳየኝ ትችላለህ?
- ት/ቤት ውስጥ የምታነቡት መፅሐፍ ምንድን ነው? የምትወደውን መገለጫ ባህርይ ብትነግረኝ? ይህን መገለጫ ባህርይ የምትወደው ለምንድን ነው?
- በት/ቤት ውስጥ ከዚህ በላይ መስራት አለብኝ የምትላቸው ነገሮች ምንድናቸው? በአነስተኛ መጠን ማድረግ አለብኝ ብለህ የምታስበውስ ምንድን ነው? ለምን?

# የሶስተኛ ክፍል ተማሪዬ እየተማረ ያለው ነገር

| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት | ሒሳብ | ሳይንስ | ማህበራዊ ሳይንስ |
|---|---|---|---|---|
| የበልግ ወቅት | ተማሪዎች ስለ ዴሞክራሲና በሶስቱ የመንግስት አካላት ላይ ስለሚያሳድረው ተጽእኖ ፣ ስለ ምርጫ ሒደትና አስፈላጊነትና በአሜሪካ ታሪክ ላይ ተጽእኖ ስለነበራቸው አንዳንድ ወሳኝ ሰዎች ይማራሉ። የአሜሪካ ሕጎች በሰዎች ሕይወት ላይ ያስከተሉትን ለውጥ በማየት ሰዎች እንዴት የዴሞክራሲ ንቁ አባላት ሊሆኑ እንደሚችሉ ይወያያሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች የአንድ ግለሰብ ተነሳሽነቶች፣ ስሜቶችና እርምጃዎች የክስተቶችን ሒደት እነዴ እንደሚቀይሩት ይማራሉ። ታሪኮችን፣ ድራማዎችን እና ግጥሞችን በማንበብ ገጸ ባህርያትን እና የ ገጸ ባህርይ ተነሳሽነቶች፣ ስሜቶች እና ተግባራት በታሪክ ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ ይተነትናሉ። | ተማሪዎች ከ2-5 እና 10 አሃዶችን በመጠቀም የማባዛትና የማካፈል መልመጃዎችን ተገንዝበው ይፈታሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ቁጥሮችን ወደሚጠጋቸው 10 ወይም 100 ለማጠጋጋት የቦታ ዋጋን ይጠቀማሉ። ተማሪዎች የቅርብ ደቂቃን አስጠግተው ሰዓት መናገር ይችላሉ፣ ስፋትና ክብደትን የሚመለከቱ የመደመርና የመቀነስ መልመጃዎችን ይሰራሉ። | ተማሪዎች የተክል እና የእንስሳት ኡደተ ሕይወትን እና የእንስሳትን ማህበራዊ ቡድን ባህርይ ይፈትሻሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች የአንድ የተወሰነ እንስሳን የተወረሱ ልዩ ባህርያት፣ ጠባይና መኖሪያ ቦታ፣ እንደዚሁም የእንስሳት አካባቢ የሚለወጥባቸውን መንገዶች ይፈትሻሉ። | ዲሲ ውስጥ ስልጣን ያለው ማነው? ተማሪዎች የዲሲ መንግስት እንዴት እንደሚሰራና በሕይወታቸው ላይ የሚያሳደረውን ተጽእኖ በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤ ለመገንባት የመንግስትን አካላት፣ ዜጎች በፖለቲካዊ ሒደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና የዲሲ አካባቢ መሪዎችን ይፈትሻሉ።<br>•••<br>የገንዘብ አስፈላጊነት ለምንድን ነው? ተማሪዎች ኢኮኖሚ ማለት ምን ማለት እንደሆነና የተለያዩ ቡድኖች ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉ እንዴት እንደሚያግዛቸው ለማወቅ ገንዘብ በሰዎች፣ በመንግስትና በንግድ ስራዎች መካከል በዕቃዎች፣ በአገልግሎት፣ በታክስና በስራ መልክ እንዴት እንደሚዘዋወር ይፈትሻሉ። |
| የክረምት ወቅት | ተማሪዎች በተለያዩ መኖሪያ አካባቢዎች፣ ለምሳሌ በጥቅጥቅ ደኖች፣ ውቅያኖች፣ በረዶ እና በአርክቲክ ዛፍ የለሽ ክልል ሕይወት ምን እንደሚመስል ይማራሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ስለ ማግኔቲዝም እና ኤሌክትሪሲቲ ጥናትና ምርምር በማድረግ በአካላዊ ሳይንስ ውስጥ ስላሉ ሃይሎች ይማራሉ። ተማሪዎች ታሪክን ለመንገር ኮሚኮች እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ይገነዘባሉ። | ተማሪዎች የ0፣1፣6-9 አሃዶችን እና የ10 ብዜቶችን በመጠቀም የማባዛት እና የማካፈል መልመጃዎችን ተገንዝበው ይፈታሉ፤ የአራት ማዕዘን ስፋትንና ከብዙ አራት ማዕዘኖች የተሰሩ ሌሎች ቅርጾችን ይዳስሳሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ክፍልፋዮችን በቁጥርነት ይረዳሉ። ተማሪዎች ስለ ክፍልፋዮች መጠን ምክንያት በመስጠት ያወዳድራሉ። | ተማሪዎች ቅሪተ አካላት ሕይወት ያላቸው ነገሮች እንዴትና የት እንደኖሩ፣ በሕይወት ለመኖር ያገዟቸው ልዩ ባህርያት ምን እንደሆኑና እንዴትስ ሊሞቱ እንደቻሉ ምን ሊነግሩን አነደሚችሉ ይፈትሻሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች በአካባቢያችን ውስጥና ዙሪያ ያሉ የአየር ሁኔታ፣ የአየር ሁኔታና የተፈጥሮ አደጋዎችን ይፈትሻሉ። | ዲሲን የቀየራት ማን ነው? ተማሪዎች የዋሽንግተን ዲሲ አመሰራረት ከሌሎች ከተሞች እንዴት እንደሚለየውና “የሃገሪቱ ርዕሰ መዲና” መሆኗ የሃገራችንን የሲቪክና ሞራል እሴቶች ለመወያየት ወሳኝ ቦታ እንዴት እንደሚያደርጋት ያውቃሉ። |
| የፀደይ ወቅት | ተማሪዎች በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ስለሚገኙ የተለያዩ ሐውልቶች፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችና አጎራባች ቦታዎች ይማራሉ። ስለ ዲሲ ታዋቂ ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶች ያላቸውን ግንዛቤ ያዳብራሉ። | ተማሪዎች ዳታን ሰብስበው በማሳየት የቅርጾችን መጠነ ዙሪያ የተመለከቱ መልመጃዎችን ይፈታሉ። | ተማሪዎች ባላንስድ፣ አንባላንስድ እና ማግኔቲክ ሃይሎች በአንድ ነገር ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ ይማራሉ። | ዲሲ ውስጥ ምርጥ የሚባለው ቦታ የት ነው? ተማሪዎች በዲሲ የመጀመሪያ ታሪክ ወቅት የነበሩ የተፈጥሮ ሐብቶችንና የዲሲ የተለያዩ ክፍሎች በጊዜ ሒደት እንዴት እንዳደጉ ያውቃሉ። |

# ከሦስተኛ ክፍል ተማሪዬ ጋር ለመለማመድ የሚረዱ እንቅስቃሴዎች

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

**በየቀኑ ለ20 ደቂቃ ያህል አብራችሁ አንብቡ።**

| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት | ሒሳብ | ሳይንስ | ማህበራዊ ሳይንስ | የማበልጸጊያ ተግባር |
|---|---|---|---|---|---|
| **የበልግ ወቅት** | ለአንድ ቀን ፕሬዚዳንት መሆን ምን ስሜት ይፈጥራል? ምን ዓይነት ተግዳሮቶች ያጋጥሙዎታል፣ ምን ዓይነት ውሳኔዎች ሊወስኑ ይችላሉ? በፕሬዚዳንት ሕይወት ውስጥ ስላለ አንድ ቀን አጭር ታሪክ ይጻፉ።<br>•••<br>መጥፎ ምርጫ ያደረጉበትን ጊዜና ከዚያም ምን እንደተማሩ በተመለከተ የግጥም ወይም የመዝሙር ግጥም ይጻፉ። አዲሱን ፈጠራዎትን (እና ትምህርትዎን) ለጓደኞችዎ ወይም ቤተሰቦችዎ ያጋሩ። | ሁለት ዳይስ ያሽከርክሩ። ስእሎችን ወይም ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም ቁጥሮችን ማባዛት ይለማመዱ።<br>•••<br>የአናሎግ ሰዓት ተጠቅመው ሰዓት መናገርን ለመለማመድ bit.ly/DCPSTellTime ይጎብኙ። | የዱር እንስሳት ሕይወትን የሚያሳይ የቲቪ ዝግጅት (Animal Planet, NatGeo, Discovery Channel) ከልጅዎ ጋር ይመልከቱና ስለሚያዩዋቸው እንስሳትና ስለሚኖሩበት አካባቢ ተወያዩ።<br>•••<br>ልዩ ባህርያት እንዴት ከወላጆች ወደ ልጆቻቸው እንደሚተላለፉ ምን እንደተማረ ልጅዎን ይጠይቁት። እናንተ የምትጋሩት ልዩ ባህርይ ምን እንደሆነና በዋነኛነት የምትለያዩበት ልዩ ባህርይስ ምን እንደሆነ ተወያዩ። | የከተማዎን ምክር ቤት አባል በኢንተርኔት ፈልገው ድረ ገጻቸውን ከልጅዎ ጋር ያንብቡ። ይህ ግለሰብ እናንተን እንዴት እነደሚወክላችሁ በመወያየት፣ የከተማ ምክር ቤት አባሉን ከከንቲባው ጋር አነጻጽሩ።<br>•••<br>ልጅዎ ስለሚያውቃቸው የተለያዩ የሰዎች ስራዎች ተወያዩ፣ ሰዎች ስራ ለምን እንደሚሰሩና ስራ እንዴት እንደሚያገኙ ተወያዩ። | ብሔራዊ መካነ እንስሳትን ይጎብኙ! የሚወድዷቸውን እንስሳት ምልከታዎችን ይመዝግቡ (ቀለም፣ ቅርጽና መጠን)። ምልከታዎችዎ በተቻለ መጠን ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያድርጉ። ለምሳሌ፣ "አንበሳው ጠይምና ጠንካራ ነው።" |
| **የክረምት ወቅት** | አሁን ከሚኖሩበት በጣም የተለየ መኖሪያ ቦታ ይምረጡ። ከአንዳንድ ምሳሌዎች መካከል በርሃ፣ ጥቅጥቅ ደን፣ ውቅያኖስ ወይም የአርክቲክ ዛፍ አልባ ክፍል ይገኙበታል። ወደ ቤተ መጻሕፍት ሄደው 2-3 መጻሕፍትን ይምረጡ። መጽሐፍቱን በመጠቀም መኖሪያ አካባቢን ዳግም ለመፍጠርና በእንስሳት መኖሪያው ውስጥ ያገኟቸውን አንዳንድ ወሳኝ ተከሎችና እንስሳት ምልክት መለ | የካርታ ስብስብ በመጠቀም ማባዛትን ይለማመዱ። ሁለት ካርዶችን በመወርወር ያባዟቸው። ሁሉም ካርዶች ባለ አስር ሊሆኑ ይችላሉ።<br>•••<br>በተጨባጩ ዓለም ውስጥ ያሉ ክፍልፋዮችን ፈልገው ይለዩ። ልጅዎ መለኪያ ማንኪያዎችና መለኪያ ኩባያዎችን በመጠቀም የተለያዩ ክፍልፋዮችን መጠን በተመለከተ ምልከታና ንጽጽር እንዲያካሂድ ያድርጉ። | ከልጅዎ ጋር የብሔራዊ ተፈጥሮ ታሪክ ሙዚየም ሲሚዝሶኒአን ትምህርት ተቋም ይጎብኙ ::<br>•••<br>ከልጅዎ ጋር በመሆን እርስዎ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ሊጎዳ የሚችል ከፍተኛ ስጋት አዘል የአየር ሁኔታን ይለዩ። እራሳችሁን ከከፍተኛ ስጋት አዘል አየር ሁኔታ ለመጠበቅ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ተወያዩ። | ከልጅዎ ጋር በመሆን በአካባቢው ወደሚካሄድ የ ANC ስብሰባ ይሂዱ ወይም ስለ ቀጣዩ የአካባቢ ምርጫ እጩ ተወዳዳሪዎች አብራችሁ አንብቡ። ለውጥ ዲሲ ውስጥ እንዴት እንደሚመጣ ተወያዩ። | ወደ bit.ly/TypingFun በመግባት አዝናኝ ጨዋታዎችና ተግባራትን በመጠቀም በኮምፒዩተር ላይ የመጻፍ ፍጥነትዎን ያሻሻሉ። ሁሉንም ጨዋታዎች ማሸነፍ ይችላሉ?<br>•••<br>Kenilworth Park and Aquatic Gardens' Water Lily and Lotus festival ይጎብኙ። ዘወትር ቅዳሜና እሁድ በ10 a.m. በኩሬው አካባቢ እንቁራሪቶችን ይፈልጉ፤ ለተጨማሪ መረጃ bit.ly/DCPSKen ይጎብኙ። |
| **የፀደይ ወቅት** | ማግኔት ማግኘት ይችላሉ? ይጠቀሙበት! በመኖሪያ አካባቢዎ የእግር ጉዞ ያድርጉ። ማግኔቱ ከምን ጋር ተጣበቀ? ለምን? አዳዲስ ግኝቶችዎን ይመዝግቡ።<br>•••<br>ከከተማ ውጭ ለሚኖር ሰው ወደ ዲሲ እንደሚጣ የሚጋብዝ ደብዳቤ ይጻፉ። በጉብኝታቸው ወቅት ስለሚያጋጥማቸው አዝናኝ ነገሮችና ታሪካዊ ቦታዎች በመጻፍ ጉብኝቱን እንዲያደርጉ ያሳምኗቸው። | አስገራሚ ጥያቄዎችን በተመለከተ ዳታ ይሰብስቡና መረጃዎን ለማሳየት ባር ግራፍ ወይም ሌሎች መነገዶችን ይጠቀሙ። ለምሳሌ፣ በፓርኩ ውስጥ ያሉ ሰዎች የለበሷቸውን ባለቀለም ቲ-ሸርቶች በተመለከተ መረጃ ይሰብስቡ። | "Rube Goldberg Machines" የሚለው ላይ የኢንተርኔተ ፍለጋ ያካሂዱ። በቤትዎ አካባቢ በሚገኙ ቁሳቁስ Rube Goldberg Machine አስመስለው ለመስራት ይሞክሩ። | በገበያ አዳራሽ (ሞል በኩል) እያሽከረከሩ ወይም የእግር ጉዞ እያደረጉ የተለያዩ ዓይነት ሐውልቶችን ለልጅዎ ያሳዩት። በኮሙኒቲዎ ውስጥ ያለ አነስተኛ ሐውልትን ጎብኝተው ልጅዎ ሐውልቱ ስለሚወክለው ሰው ወይም ክስተት ጥያቄዎችን እንዲያመነጭ ይጠይቁት። | Kenilworth Park and Aquatic Gardens' Water Lily and Lotus festival ይጎብኙ። ዘወትር ቅዳሜና እሁድ በ10 a.m. በኩሬው አካባቢ እንቁራሪቶችን ይፈልጉ፤ ለተጨማሪ መረጃ bit.ly/DCPSKen ይጎብኙ።<br>•••<br>የበጋ ወቅት ዕቅዶችዎ ምን ምን ናቸው? በበጋው ወቅት መማራሁን ለመቀጠል በጋራ ልትሰሯቸው የምትችሉ አምስት ተግባራት ላይ ጥልቅ የሃሳብ ልውውጥ አድርጉ። |

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት — ሒሳብ — ሳይንስ — ማህበራዊ ሳይንስ — የማበልጸጊያ ተግባር